# በንዋያተ ቅድሳት ላይ የሚታዩ ለውጦች

**ፍሬህይወት ባዩ**[1]

**አጽኅሮተ ጽሁፍ**

ይህ ጥናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ) እየተገለገለችበት ያሉ ንዋያተ ቅድሳት ለውጥ ላይ ያተኩራል። የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት አጥኚዋ ቀደም ሲል ንዋያተ ቅድሳት ላይ ጥናት ስታካሂድ በየጊዜው ለውጥ በማየቷ የለውጡን ምክንያትና አይነት በማስረጃ ለማመላከት ከመነጨ ፍላጎት ነው። የጥናቱ አላማ በንዋያተ ቅድሳት ላይ የታየውን ለውጥ ማሳየት ነው። ለጥናቱ ግብአት የሆኑ ቀዳማይ መረጃዎች በአዲስ አበባ አህጉረ ስብከት ከሚገኙ ሁለት የኢ.ኦ.ተ. አብያተ ክርስቲያናት የተገኙ ናቸው። የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴው ቃለ-መጠይቅና ምልከታ እንዲሁም የሰነድ ፍተሻ ነው። ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉት ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን እና በውስጡ ያሉ የቤተክርስቲያኗ የአምልኮ መፈጸሚያ ቁሶች፣ በአጸድ ውስጥ የሚገኙና ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶችነሰ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ቁሶች እንዲሁም የጳጳሳት ልብሶችን ይጨምራል። የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳት ቀደም ባለው ዘመን በሀገር ውስጥ ባለሙያ እና በአካባቢው በሚገኝ ቁሶች የሚሰሩ ነበሩ። ሆኖም ይህ ትውፊት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣት በከፊል ከውጭ ሀገራት በሚመጡ ጥሬ እቃዎች እየተተኩ ይገኛሉ። ጥቂቶቹም ሙሉ በሙሉ ከውጭ ሀገራት ተሰርተው የሚመጡ ንዋያተ ቅድሳት እየበረከቱ መምጣት ከታዩት ለውጦች መካከል አብዛኛውን ቦታ የሚይዙ ናቸው።

## 1. መግቢያ

በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው ንዋያተ ቅድሳት የኢ.ኦ.ተ.ቤ በሆኑት ላይ ነው። "ንዋየ ቅድሳት እንደ አልባሳት፣ ፃህል፣ ፅዋ ፣ ... ያሉ በኣብያተክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ የተቀደሱ እቃዎች" (የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ 2006፡ 295-296) ናቸው። በዚህ መሠረት ንዋያተ ቅድሳት ለሃይማኖት ተግባር የሚውሉ ቁሶች ናቸው። ቁሶቹ ሲሰሩ ከምን እንደሚሰሩና ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ በመጽሐፍ ቅዱስ[2] እንዲሁም በተለያዩ በኢ.ኦ.ተ.ቤ በተጻፉ እና በምትቀበላቸው መጽሐፍት ውስጥ ተዘርዝረው ይገኛሉ። የንዋያተ ቅድሳቱ አሰራር መነሻ ሀሳቡ መጽሐፍ ቅዱስ ሆኖ ሀገረ-ሰባዊውን እውቀት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ግለሰቦች በአካባቢያቸው በሚያገኙት ጥሬ እቃ ይሰሯቸዋል።

የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ለአምልኮ ተግባር የምትገለገልባቸው ንዋያተ ቅድሳት ለማጥናት መነሻ ምክንያቱ አጥኚዋ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ጥናት ስታደርግ በንዋያተ ቅድሳቱ ላይ በየጊዜው

---

[1] አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የስነጽሁፍና ፎክሎር ተመራማሪ፡፡

[2] በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ንዋያተ ቅድሳትን በተመለከተ በተለያዩ ቦታዎች ተገልጿል። ከእነዚህ መካከል ለምሳሌ ዘፀ.25፣ 19፤ 37፣ 7፤ 40፣ 8። 1ኛ ነገ.6፣ 23፤ 7፣ 23-36። 2ኛ ነገ.6፣2-7። ሕዝ. 9፣ 3፤ 10፣ 3 እና ሄኖክ 14፣ 11 ይገኙበታል።

የሚታዩትን ለውጦች በማስተዋል የለውጡን አይነትና ምክንያት ለመመርመር ከመነጨ ፍላጎት ነው። ጥናቱ በዋነኝነት የሚመልሰው ጥያቄ፤ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳት ለታየባቸው ለውጥ ምክንያቱ ምንድን ነው? የሚል ነው። የጥናቱ ዋና አላማ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳት በሂደት የታየባቸውን ለውጥ ምክንያቱን ጨምሮ ማሳየት ነው። ዝርዝር አላማዎቹ፤ ለውጥ የታየባቸው ንዋያተ ቅድሳት ማሳያ ማቅረብ እንዲሁም የንዋያተ ቅድሳቱን የለውና ምክንያቱን መግለጽ የሚሉ ናቸው። የጥናቱ ጠቀሜታ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳት ከሃይማኖታዊ ፋይዳቸው ባሻገር የሀገርን የቁሱ ሰሪዎች ጥበብ እንዲሁም ሀገረሰባዊው እውቀት በሂደት ያሳየውን ለውጥ ማሳያ ነው።

የጥናቱ ዘዴ ገላጭ ስልትን የተከተለ ነው። መረጃው ወደ መስክ በመሄድ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ በቃለመጠይቅ እንዲሁም በምልከታ ዘዴ ተሰባስቧል። ቀዳማይ መረጃ የተገኘባቸው ቦታዎች በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም እና ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ንዋያተ ቅድሳት በሁሉም የኢ.ኦ.ተ.ቤ ተመሳሳይ ቅርጽ እና ተግባር ያላቸው ቢሆንም ሁለት ኣብያተ ክርስቲያናትን መምረጥ ያስፈለገበት ምክንያት የንዋያተ ቅድሳቱን ለውጥ አነጻጽሮ ለማየት እንዲያመች ነው፡፡ ለምርጫው ታላሚ ናሙና (ታርጌት ሳምፐሊንግ) እንዲሁም የምቾት ናሙና አገልግሎት ላይ ውለዋል። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሙዝየሞች አሏቸው። ስለዚህ ሙዝየሞቹ ውስጥ የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት ለማንኛውም ተመልካች እና አጥኚ በቀላሉ ለማግኘት ምቹ በመሆናቸው እነዚህን ሁለት ቤተ-ክርስቲያን የጥናቱ አካል ሆነው እንዲመረጡ ምክንያት ሆኗቸዋል። አገልግሎት የማይሰጡ ንዋያተ ቅድሳትም በአብያተ ክርስቲያናት እቃ ቤቶች ይቀመጣሉ። ሆኖም ለዚህ ጥናት መረጃ ከተመረጡ ሁለት አብያተ ክርስቲያን ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን እና ርእሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን በእቃቤቶች ከሚያስቀምጧቸው በተጨማሪ ቀደም ሲል ያገለግሉ የነበረ እና ከተለያዩ ሀገራት እና ታዋቂ ሰዎች በስጦታ የተሰጡ ንዋያተ ቅድሳት በሙዝየሞቻቸው ውስጥ ይገኛሉ[3]። የንዋያተ ቅድሳትን ለውጥ ለመረዳት የቀድሞዎችን ዛሬ አገልግሎት በመስጠት ላይ ከሚገኙት ጋር አነጻጽሮ ለውጡን በቀላሉ ለመለየት የላቀ ሚና አላቸው። ኣብያተ ክርስቲያናቱ ሙዝየም ያላቸው መሆኑ ታላሚ ናሙና ሲሆን ቅርብ መሆናቸው ደግሞ የምቾት ናሙና ነው። በሁለቱም አብያተ ክርስቲያን ከሚያገለግሉ ካህናት ሁለት፣ ሁለት ካህናት በአጠቃላይ አራት ካህናትና ሁለት ሊቃውንተ ቤተ-ክርስቲያን በአጠቃላይ ስድስት መረጃ አቀባዮች መረጃ በመስጠት ተሳትፈዋል። ለመረጃ አቀባይነት የተመረጡት ካህናት በንዋያተ ቅድሳቱ ዘርፍ የሚያገለግሉ በመሆናቸው የተሻለ እውቀትና ልምድ ይኖራቸዋል በሚል እሳቤ ነው፡፡ ሁለቱ ሊቃውንት በንዋያተ ቅድሳት ላይ መጽሐፍ የጻፉና የተሻለ እውቀት አላቸው በሚል በጥቆማ የተመረጡ ናቸው።

---

[3]በሁለቱ ሙዝየሞች ውስጥ የሚኅበኙት ቅርሶች በአብዛኛው ንዋያተ ቅድሳት የነበሩ ናቸው። በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ይገኛሉ። በሙዝየሙ ውስጥ የሚገኙ ቅርሶች፤ ከተለያዩ ነገሥታትና ግለሰቦች የተሰጡ የወርቅ እና የብር መስቀሎች፣ ካባዎች፣ መጐናጸፊያ፣ ድባብ፣ ጥላ፣ አክሊሎች፣ ጽና፣ ፀናፅል፣ ማኅፈዳት፣ ሥዕል፣ ዕርፈመስቀል፣ መሶበወርቅ፣ እጣንማቅረቢያ፣ የብራና መጻሕፍት፣ መቅረዝ ከሩሲያ መንግሥት ለቅዱስጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የተሰጠ ደወልና ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት እንዲሁም የነገሥታት መገልገያ ቁሳቁሶች፣ የተለያዩ ፎቶዎችና ሌሎችም ቅርሶች በሙዝየሙ ውስጥ ይገኛሉ። ለአጼ ምኒልክ ከተለያዩ ሀገራት የተሰጡ ስጦታዎች፣ አፄምኒልክ፣ንግሥት ዘውዲቱና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለቤተክርስቲያኗ ያበረከቱት ንብረቶች፣ እቴጌ ጣይቱ እንዲሁም አፄምኒልክ ለአድዋ ጦርነት ሲዘምቱ የያዟቸው የጦርመሣሪያዎች፣ የተለያዩ እቃዎች፣ የነገሥታቱ ልብሳሶቻቸው፣ ነጋሪት እና ሌሎችም አሉ፡፡

መረጃ ለማግኘት ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና የሰነድ ምርመራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ንዋያተ ቅድሳቱን በተለይም ለእይታ የተፈቀዱ እና በሙዝየም የሚገኙትን እንዲሁም በእቃቤቶች ያሉ እና በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙትን በመመልከት መረጃ ተሰብስቡዋል። በምልከታ ወቅት የተፈጠሩ ጥያቄዎችንና ስለንዋያተ ቅድሳቱ እውቀት ያላቸውን ካህናትና ሊቃውንት ጥያቄ በማዘጋጀት በቃለመጠይቅ ዘዴ የጥናቱ ግብአት የሆኑ መረጃዎች ተገኝተዋል። ስለ ንዋያተ ቅድሳት ምንነት አሰራር መመሪያና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ከተጻፉ ሰነዶች በማንበብ በቃለመጠይቅ እና በምልከታ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማናበብ ጥናቱ ተከናውኗል።

ንዋያተ ቅድሳቱ የተጠኑበት የጽንሰ ሀሳብ መነሻ ፎክሎር ነው። ከፎክሎር የጥናት ዘርፎች መካከል በተለይ የቁሳዊ ባህል ጥናት ለዚህ ጥናት የጽንሰ ሀሳብ መነሻ በመሆን አገልግሏል። የቁሳዊ ባህልንና የንዋያተ ቅድሳትን ተያያዥነት አስመልክቶ በቀጣዩ ክፍል እንመለከታለን።

## 2. ፎክሎር እና ንዋያተ ቅድሳት

ንዋያተ ቅድሳት በፎክሎር ጽንሰ ሀሳብ ከሚጠኑ አበይት ዘርፎች መካከል በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ይመደባሉ፡፡ ቁሳዊ ባህል በዐይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ፣ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ከመፈጠሩ አስቀድሞም የነበረ ነው። የቁሳዊ ባህል ጥናት የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች የተሠሩበትን ዘዴ እና ተያያዥ በሆኑ እሴቶች ላይ በማተኮር የሚያጠና የጥናት ዘርፍ ነው። ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በቃሉ ላይ ብያኔ የሰጡ ሲሆን በተለይ ስፋቱንና ጥልቀቱን በማሳየት ረገድ በመስኩ የተለያዩ ጥናቶችን ያከናወኑት "Henery Glassie" ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው። ከሰጡት ሰፊ ብያኔ በጣም ጥቂቱን ብንመለከት፣ "ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ ለተለያየ አገልግሎት ሊያውለው በእጁ ያበጀው እቃ ነው። እቃው ከቁስነቱና ከሚሰጠው አገልግሎት ባሻገር የቁሱን ሰሪዎች ወይም የባለቤቶቹን አተያይ፣ የህይወት ፍልስፍና ጭምር የያዘ ነው" (Glassie 1999፣ 42) የሚል ይገኝበታል።

በቁሳዊ ባህል የጥናት ዘርፍ ከሚጠኑት ቁሶች ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅ ሥራ፣ ሀገረሰባዊ ሥዕል ሀገረ-ሰባዊ ምህንድስና እና ሀገረሰባዊ ልብስ ይገኙበታል (Dorson 1972፡ 232)፡፡ የንዋያተ ቅድሳትን ቁሳዊ ባህል ገጽታ ስንመለከት ትኩረታችን አሠራራቸው የሚሠሩበት ጥሬ እቃ ሀገረ-ሰባዊነታቸው ላይ ማተኮሩ አንዱ ነው። ከእነዚህም ለአምልኮ መፈጸምያ የሚውሉ እቃዎች ይገኙበታል፡፡ ንዋያተ ቅድሳቱ ከቁስነታቸው እና እንደማንኛውም እቃ ለአገልግሎት ከመዋላቸው ባሻገር በሃይማኖት ዐይን የሚታዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሳዊ ሀብቶች የሚሰሩበት ቅርጽ እና የመሰራታቸው ምክንያት ሃይማኖታዊ ሲሆን ቁሱን የሚሰሩት ግለሰቦች እውቀት ደግሞ ትውፊታዊውን መንገድ የተከተለ ነው። በተለይ የባለሙያዎቹ የእውቀት ሽግግር ትውፊታዊ ነው። ለምሳሌ አንድ ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ነው። ህንጻ ቤተክርስቲያኑን የሚሰሩ ባለሙያዎች ግን ያንን የሚመስል ማንኛውንም ቤት መስራት የሚችሉ ባለሙያዎች ናቸው። ስለዚህ ትውፊታዊው እውቀት ከንዋያተ ቅድሳቱ ጋር የሚያያዘው በሰሪዎቹ ጥበብ፣ በሚሰሩበት ጥሬ እቃ እና እውቀቱ በሚሸጋገርበት ስልት ነው።

የኢ.ኦ.ተ.ቤ የሃይማኖቱ መሰረታዊ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይቃረኑ ትውፊቶችን በመቀበል ከዘመን ዘመን ሲሸጋገሩ ቆይተዋል። የትውፊትን እና የሃይማኖትን አለመቃረን አስመልክተው፤ "ትውፊት ከጥንት ጀምሮ በቤተ-ክርስቲያን በኩል በቃል ሲነገር የመጣ። በቃልም በጽሑፍም ከአበው ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረና የሚኖር ማለት ነው፡ ፡ ...ትውፊት ከቅዱሳን መጻሕፍት ጋር የሚቃረን አይደለም" (ነጋሽ፣ 1988፡ 35)፡፡

ለሃይማኖት ተግባር የሚውሉ እቃዎች ከመሰል እቃዎች ተለይተው ንዋያተ ቅድሳት የተባሉበት ምክንያት ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት በሃይማኖቱ ሥርዓት መሠረት በሚደረግላቸው ጸሎት እና በሚቀቡት ቅብዐ ቅዱስ ስለሚቀደሱ ነው። እያንዳንዱ ንዋየ ቅድሳት ተሰርቶ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት በሃይማኖቱ ስልጣን በተሰጠው ሰው ተገቢው ጽሎት ይደረግበታል። ለምሳሌ ከንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ለሆነው ለእርፈ መስቀል የሚጸለየውን እንመልከት፣

> አሁንም የአንተ በምትሆን በዚህች ቅድስት እርፈ መስቀል ላይ ስልጣንህን አሳድር፣ ባርካት፣ አክብራት፣ ኃይልንም ስጣት። ከንፈሮቹን ባነጻህለት በነቢዩ በኢሳይያስ ዘንድ እንደተደረገው ከሚያገለግሉት ከቅዱሳን መላእክት ዘንድ ለተገኘች ለሱራፌ ጉጠት ኃይልን እንደሰጠሀት እኛም ደምህን ለአገልጋዮችህ ለማቀበል በሚገባ በንጽህና ሆነን ከልጅህ ፊት እንድንቆም። ስለዚህም ሰው ወዳጅ ሆይ የበጎነትህን ቸርነት እንለምናለን እንማልዳለን። የከበረች ይህቺን ዕርፈ መስቀል ባርካት አንጻት ክቡር ደምህንም ሙላት ክብር ምስጋና ገንዘቡ የሚሆን የአንድ ልጅህን ደም ለመቀበያ የተመረጠ ንጹህ እቃ ትሆን ዘንድ አሜን። ኃይልንም ምላት የተመረጠችም አድርጋት ይህችን መንካ አንጻት አሜን (ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ምእራፍ 1፣ ቁ 11-15)።

ትውፊታዊውን እውቀት መሠረት አድርጎ የተሰራውን እቃ በኢ.ኦ.ተ.ቤ ጸሎት ተደርጎ ቅባ ቅዱስ በመቀባት ከማንኛውም መሰል ቁስ ተለይቶ ስሙ ንዋየ ቅድሳት ይባላል። የንዋያተ ቅድሳቱ ተግባርም ሃይማኖታዊ ብቻ ይሆናል። ንዋያተ ቅድሳት እንዴት እንደሚሠሩ፣ ከምን እንደሚሰሩ፣ ለምን የያዙትን ቅርጽ እንደያዙ፣ ቀለማቸው ምሳሌያቸው በአገልግሎት ወቅት ማን መቼና እንዴት? መገልገል እንዳለበት ዝርዝር ሕግና ምሳሌያቸው ጭምር በጽሑፍ ሠፍሮ ይገኛል (ፍትሐነገሥት.መን.አን.12)፡፡

ንዋያተ ቅድሳቱ ለአገልግሎት ብቻ ተብለውየሚሠሩ ሳይሆን አሠራራቸው፣ የሚሰሩበት ጥሬ እቃ፣ መጠናቸው፣ ቅርፃቸው፣ የሚቀመጡበት አቅጣጫ፣ ብዛታቸው፣ ቀለማቸው፣ የሚገለገሉባቸው ግለሰቦች እና ሌሎቹም ሃይማኖታዊ ተምሳሌት እና ፍቺ አላቸው (ያሬድ፣ 1996፡ 59)፡፡

**2.2 ለውጥ የታየባቸው ንዋያተ ቅድሳት**

ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉት በርካታ ሲሆኑ ቁጥራቸው ከአርባ በላይ ነው። በጥቅሉ ህንጻ ቤተክርስቲያኑ እንዲሁም በውስጡ የሚገኙ መገልገያዎች ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን፣ ጉልላት ሻኩራዎች፣ በአጸድ ውስጥ የሚገኙ ቤተ-ልሔም፣ ግብር-ቤት፣ ክርስትና-ቤት፣ ደወልና ሌሎችም የህንጻ ቤተክርስቲያኑ የውጨኛው አካልና በግቢ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

በህንጻ ቤተክርስትያን የውስጥ ክፍሎች የሚገኙትን ስንመለከት ወደ ውስጥ ሲገባ መጀመሪያ የሚገኘው ክፍል ቅኔ ማሕሌት ነው። በዚህ ክፍል የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት ለመዝሙር አገልግሎት የሚውሉት ከበሮ፣ ጸናጽል እና መቋምያ ሲሆኑ ለመዝሙር አገልግሎት ከሚውሉት ውጭ ሥእል፣ መጻሕፍት፣ አትሮንስ፣ ቃጭል፣ መቅረዝ እና መጋረጃ ይገኙበታል። በመቅደስ አገልግሎት የሚሰጡ ንዋያተ ቅድሳት በርካታ ናቸው። እነዚህም፤ ታቦት፣ ልብሰ ተክህኖ፣ መንበር፣ ጽዋዕ፣ እርፈመስቀል፣ ጻህል፣ ዐውድ፣ አጎበር፣ መነሳነስ (ጭራ)፣ መሶበወርቅ፣ ብርት፣ ሰን፣ ጽንሐሕ፣ ሙዳይ፣ መኀናጸፊያ፣ ቀጸላ፣ ቃጭል፣ መስቀል (የመጾርመስቀል)፣ ማህፈድ እና ሌሎችም ይገኙበታል። በተጨማሪም በየክፍሉ እየተዘዋወሩ ለምሳሌ እንደ ጥላ እና ቃጭል አገልግሎት የሚሰጡ ንዋያተ ቅድሳትም አሉ። በቀጣዩ ንኡስ ርእስ ከንዋያተ ቅድስቱ መካከል ሀገረሰባዊውን እውቀት መሠረት አድርገው ከሚሰሩት መካከል በሂደት ለውጥ የታየባቸውን እንመለከታለን።

ትውፊታዊ እውቀትን መሠረት አድርገው የሚሰሩ ንዋያተ ቅድሳት በርካታ ናቸው። ከእነዚህ መካከል አሰራራቸው ትውፊታዊ እውቀትን የተከተለ ስለመሆኑ ማሳያ የሚሆኑ ጥቂት ምሳሌዎችን ከሀገረሰባዊ እጅ መስራ፣ ከሀገረሰባዊ ሥዕል፣ ከሀገረሰባዊ ምህንድስና እና ከሀገረሰባዊ ልብስ እንመለከታለን።

ከሀገረሰባዊ እጅ ሥራ መሶበ ወርቅ እና ሙዳይ ለማሳያነት ምሳሌነት ተመርጠዋል። መሶበ ወርቅ አገልግሎቱ ዲያቆኑ ህብስቱን ከቤተልሔም ወደ ቤተመቅደስ የሚወስድበት ነው። ሙዳይ ለቤተ-ክርስቲያን ማእጠንት የሚሆን ዕጣን የሚቀመጥበት ንዋየ ቅድሳት ነው። ሙዳይም ሆነ መሶበ ወርቅ በተመሳሳይ ጥሬ እቃ እና የአሰራር ስልት ይሰራሉ። ሙዳይም ሆነ መሶበ ወርቅ የሚሰሩት ከአክርማ ወይም ከስንደዶ ነው። አክርማው ክረምት እንደ ወጣ መስከረም መጨረሻና ጥቅምት መጀመሪያ (እንደ አካባቢው ሊለያይ ይችላል) ይቀጫል ወይም ይለቀማል፡፡ ከተቀጨ በኋላ ከፊሉ መስፊያ የሚሆነው ይሰነጠቃል፡፡ ሰበዝ የሚሆነው ድፍን ይሆናል። ስንጥቁም ድፍኑም እንዲደርቅ አመቺ በሆነ ቦታ በአብዛኛው  በቤት ጣራ ላይ ታስሮ ይሰቀላል፡፡ የተሰነጠቀው የተለያየ ቀለም እንዲኖረው ከተፈለገ ከዕፅዋት የተዘጋጀ ቀለም ውስጥ ይነከራል፡፡ ያልተነከረው ነጣ ያለ መልክ አለው። ሲሰፋም ድፍኑ ከውስጥ ሆኖ ስንጥቁ ከላይ መስፊያ ይሆናል፡፡ መስፊያውን ለማስገባት ለመብሻ የሚያገለግለው ወስፌ ይባላል፡፡ ወስፌ መያዣው የእንጨት ሆኖ ጫፉ የሾለና ቀጭን ብረት ነው፡፡ ሙዳይም ሆነ መሶበ ወርቅ በአብዛኛው በሴቶች ይሰፋሉ፡፡

በሙዳይ እና በመሶበ ወርቅ ላይ የታዩ ለውጦች ዋናው ምክንያት የሚሰራሩት ቁስ መለወጥ ነው። በተለይ ከላይ እንዳየነው በስንደዶ ይሰራ የነበረው ሙዳይ በብረት ነክ ማእድናት እንዲሁም በፐላስቲክ መሰራት መጀመሩ ነው።  ያለዘመናዊ ማሽን በእጅ ይሰራ የነበረው በዘመናዊ ማሽን መሰራቱም የለውጡ አካል ነው።

የቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረት ከሆነው አንዱ ሀገረሰባዊ ምህንድስና ነው። ከንዋያተ ቅድሳት መካከል የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሰራር እንደምሳሌ መታየት የሚችል ነው። በንዋያተ ቅድሳቱ ላይ የቅርጽ ለውጥ ከታየባቸው አንዱ የሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሰራር ይገኝበታል። ለምሳሌ አንዱ

የህንጻ ቤተ-ክርስቲያን ቅርጽ የሆነው ሰቀላማ የህንጻ ቤተ-ክርስቲያን አሰራር ነው። ሰቀላማ የህንጻ ቤተ-ክርስቲያን ቅርጽ ጥንት ከኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ሕንጻ አሠራር አንዱ ነበር፡፡ ዛሬ ግን አልፎ አልፎ ቢገኝ እንጂ ቀርቷል።[4] የህንጻ ቤተ-ክርስቲያን የውስጥና የውጭ ቅርጽ ሃይማኖታዊ ተምሳሌት እንዲኖረው ተደርጎ ይተረጎማል። “ሕንጻ ሲታነጽ ምስጢር እንዳይፋለስ፣ አሠራሩ ትርጉም አልባ እንዳይሆን አበው ይጠነቀቁበታል፣ ከቅዱሳን መላእክት አገልግሎትና ተጋድሎ ጋር እንዲያያዝ ሆኖ ይሰራል” (ያሬድ፣ 1996፡ 47)፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታነጹ የቤተ-ክርስቲያን ህንጻዎች ለማንኛውም ተመልካች ማየት እንደሚቻለው ቀድሞ የነበራቸው ቅርጽም ሆነ የሚሰሩበት ጥሬ እቃ ሙሉ በሙሉ ተለውጧል። አብያተ ክርስቲያናት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቆርቆሮ (በግንብ) ከመሠራታቸው በፊት ይሰሩ የነበረው በሣር ክዳን፣ በእንጨት፣ ማያያዣቸው ልጥ ሲሆን፣ ግድግዳው አፈር(ጭቃ) ነበር፡፡ ሠሪዎቹ በአካባቢው ያሉ ምእመናን እንዲሁም ካህናት ናቸው። የሚሰራበት ጥሬ እቃ እና የአሰራር ቅርጹ መለወጥ ከቅርጽ እና ለመስሪያ ከሚገለገሉበት ጥሬ እቃ ባለፈ ለአሰራር ቅርጹ እና ለቁሱ የሚሰጠው ሃይማኖታዊ ምሳሌ አብሮ ይቀራል። ለምሳሌ ቀድሞ የነበረ አሁን በሚሰሩት ሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ላይ ቦታ የሌለው ጉልላት፣ ሻኩራ እና በጉልላቱ ላይ ይደረግ የነበረው የሰጐን እንቁላል ወይም ብረትነክ ማእድን ይገኝበት ነበር። የሰጐን እንቁላል በሃይማኖት ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የሃይማኖቱ ማስተማሪያ ተምሳሌትም ነው።

Ballenger አንድ ለሃይማኖታዊ ተግባር የሚውል ቁስ ከቁስነቱ ባሻገር ያለውን ጠቀሜታ ሲገልጹ፣ “የአንድ ቁስ አገልግሎቱ ሞራላዊ ወይም መንፈሳዊ እውነትን ወክሎ መቆም ነው” (1988፣ 769)። በማለት ከሚታየውና ከሚዳሰሰው ቁስ ባለፈ የማይታይ ሃይማኖታዊ ፍች እንዳለውም ጭምር ይላሉ። በኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋየተ ቅድሳት ላይ የታየው የህንጻ ቤተ ክርስቲያን የቅርጽ ለውጥ ሲጠፋ ከቅርጽ ባሻገር ተምሳሌቱም አብሮ ይጠፋል። በህንጻ ቤተ ክርስቲያን ላይ የመጣው ለውጥ ከሚሰራበት ቁስ እና ከአሰራሩ ቅርጽ ባለፈ የሰሪዎቹን ሀገረሰባዊ እውቀትም አብሮ እንዲጠፋ ብሎም እንዲከስም የሚያደርግ ነው። ዘመናዊውን የሕንጻ አሰራር ጥበብ የተማሩት ሲመጡ ሀገረሰባዊው እውቀት ለዘመናዊው መሠረት ሳይሆን ይረሳል። ሙያው የያዛቸውን እሴቶች ጨምሮ ለቀጣዩ ትውልድ ሳይሸጋገር ከባለሙያዎቹ ጋር አብሮ ያልፋል።

ከቁሳዊ ባህል ጥናት አንዱ ሀገረሰባዊ ልብስ ነው። ንዋየተ ቅድሳት ከሆኑት ልብሶች መካከል ካህናት እና ዲያቆናት በአገልግሎት ወቅት የሚለብሷቸውና የጳጳሳት ልብሶች ይገኙባቸዋል። እነዚህ ልብሶችም የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትውፊታዊውን መንገድ ተከትለው የሚሰሩ ነበሩ[5]። ቀደም ሲል በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ካህናትና ዲያቆናት ይለብሷቸው የነበሩ ልብሰ ተክህኖ ከጥጥ በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች የሚዘጋጁ ነበሩ። ዛሬ ሙሉ በሙሉ ከቆዳም ሆነ ከጥጥ ሀገረሰባዊውን የአሰራር ጥበብ ተከትሎ የሚሰራ የልብሰ ተክህኖ የለም። ቀድሞ በሀገረሰባዊው ቁስና እውቀት ከጥጥ የተሰሩ ተክህኖ ልብሶች በጥቂት አብያተክርስቲያናት ዕቃቤቶች ውስጥ ይገኛሉ[6]፡፡ አሁን

[4]ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ (ቃለ መጠይቅ)።

[5]ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ (ቃለመጠይቅ)።

[6]ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ (ቃለመጠይቅ)።

አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት ልብሰ ተክህኖ ሙሉ በሙሉ በፋብሪካ በሚሰሩ የተለያዩ ጨርቆች ተተክተዋል። አብዛኞቹ በሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች የሚመረቱ ሳይሆኑ በውጭ ሀገራት ተመርተው በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ተሰፍተው የሚዘጋጁ ናቸው።

ይህም የልብሰ ተክህኖን ለውጥ በተመለከተ ለዚህ ጥናት ምልከታ ሲደረግ በተደጋጋሚ የታየ ነው። የልብሰ ተክህኖን ለውጥ አስመልክቶ በጽሑፍ ከሰፈሩ ማስረጃዎች መካከል ለምሳሌ፤ "በግዢ በመባዕና በሥዕለት መልክ ወደ ቤተ-ክርስቲያን የገቡ የአንዳንድ ልዑካን ልብስ አሰፋፍና ቀለሞቻቸው በየጊዜው እየተለዋወጡ ነው" (ሐመር፣ ሐምሌና ነሐሴ፣ 1994፡ 13)። በማለት ከጊዜ ወደ ጊዜ ልብሶቹ የሚታየውን ለውጥ ይገልጻሉ።

የቁሳዊ ጥናት ትኩረት ከሆነው መካከል ሌላኛው ሀገረ ሰባዊ ሥዕል ማለትም ስዕለ ቅዱሳን ነው። ቀደም ባለው ጊዜ በኢ.ኦ.ተ.ቤ የሚታወቀው ሥዕል በሰአሊያን የሚሳሉ ስዕላተ ቅዱሳን ብቻ ነበሩ። በዘመን ሂደት በዘመናዊ ኢንዱስትሪ መስፋፋት የመጣው የወረቀት ሥዕል በእጅ የሚሳለውን ሥዕል ቦታ እየተካ ይገኛል። ቅዱሳን በሁሉም አብያተ ክርስቲያን ባይሆንም ዛሬም ብዙ አብያተ ክርስቲያን የውስጥ ግርግዳዎች በጣራው የውስጠኛው ክፍል ላይ እንደ ቀድሞው ይሳላሉ። በህንጻ ቤተ-ክርስቲያን ግርግዳ ላይ ከሚሳሉት በተጨማሪ በብራና መጻህፍት ላይ መሳል የተለመደ የቤተክርስቲያኗ ትውፊት ነው። ሥዕሉን ለመሳል የሚጠቀሙባቸው ቁሶች በአካባቢያቸው በቀላሉ የሚያገኟቸው ቀለም፣ ብሩሽ፣ ጨርቅ እና ማጣበቂያ ናቸው፡፡ ቀለማቱ የተለያየ መልክ እንዲኖራቸው የተለያዩ ጥሬ እቃዎችን ይጠቀማሉ። ሥዕል ለመሳል አስፈላጊ የሆኑትን ግብአቶች እና ከምን ከምን ይዘጋጁ እንደነበር በጽሁፍ ከሰፈረ ዝርዝር ውስጥ ለማሳያ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን እንመልከት።

> *በመጀመሪያ እንጨት ተጠርቦ ይሾላል፣ ከዚያም ከሾለው እንጨት ላይ ከአህያ ጋማ የተቆረጠ ጠጉር በክር ይታሰርበትና በቁልቋል ደም ይጣበቃል፣ የአህያው ጸጉርም እንዳይፈታ ያደርገዋል፣ ይህም ብሩሽ ሆኖ ይሳልበታል፡፡ ጨርቁም ከጥጥ በፈታይ አማካይነት ተዘጋጅቶ፣ በሸማኔ የሚሰራ ነው፡፡ ግርግዳውና ጨርቁ የሚጣበቅበት ማጣበቂያ በቤት ውስጥ የሚዘጋጅ ነው። ይሄውም የቀይ ጤፍ ወይም የስንዴ ዱቄት በውሃ ቀጠን ብሎ ይበጠበጥና በእሳት ላይ ተጥዶ ይፈላል፡፡ የፈላው ሲበርድ ግርግዳውና ጨርቁ ተቀብቶ ይጣበቃል፡፡ ሙጫ ለብራና ሥዕል አንድም ለሐረግ ቀለማት መበጥበጫና ወዝ መስጫ ያገለግላል፡፡ የግራር ሙጫ ከውሃ ደባልቆ በጸሀይ ወይም በእሳት ቀልጦ ለብራና ሥዕል ከቀለማት ጋር ይደባለቃል፡፡ የቁርበት ማሸጊያ ከእንቁላል ጋር ተደባልቆ ለቀለማት መበጥበጫና ማድረቂያ የሚሆን ነው፡፡ ዝግጅቱም የከብት ቆዳ በደንብ ታጥቦ ይተለተላል። የተተለተለውም በሸክላ ይቀቀላል፡፡ በደንብ ሲነፍር (ሲበስል) በማጣሪያ ይጣራል፡፡ የተጣራው ውሃ በዕቃ ተደርጎ በቀዝቃዛ ቦታ ይቀመጣል፡፡ የተቀመጠውም ይረጋል፡፡ በደንብ ከረጋ በኋላ ይያያዛል፡፡ የተያያዘው በቢላዋ ተከፋፍሎ ሳንቃ ላይ ተደርጎ ይደርቃል፡፡ ለሥራ በተፈለገ ጊዜ በሚያስፈልገው መጠን እየተበጠበጠ ይሠራበታል፡፡ አገልግሎቱ የሥዕሉን ጨርቅ ግድግዳ ላይ ለመለጠፍ ከስንዴው ሙቅ ጋር ተደባልቆ መለጠፊያ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ለቀለም መሥሪያ (ለዓይነት)*

ይጠቅማል፡፡ የዕንቧይ ውሃ የተለያዩ ነፍሳት ቀለሙን እንዳይበሉት ለመከላከል ከቀለማት ጋር ይደባለቃል፡፡

ከሥዕል ጋር ተያይዞ ሙያዊ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ለምሳሌ ናዞርድ የቀለም ስም ሲሆን ሰማያዊ ማለትነው፡፡ ነጠብጣብጌጣጌጥ ማለት ነው፡፡ ለሂ- ማለት ውብት ሰጭ ማለት ነው። ከአንገት በላይ የሚያሳይ ሥዕልን ጉርድ ይሉታል፡፡ እያንዳንዱ የሚያሳየውን አካል የሚያሳይ ከሆነ ማዋዛት ሲሉት መሥራት ወይም መሣል ለማለት ደግሞ ሐረግ መጣል ይሉታል፡፡ የብርሃንን አቅጣጫ ተከትሎ የሥዕሎችን ክብነት የሚያሣይ ሥዕል ከሆነ ብሩህና ጥላ ይባላል፡፡ ሥዕል ያላረፈበት ትርፍ ሰሌዳ ካለ ደግሞ መዳብ ይባላል (ሀብተማርያም፣ 1963፡ 268-271)፡፡

ሥዕሉ የጌታ ስቅለት፣ የቅዱሳን፣ የመላእክት እየተባለ አቅጣጫቸው የቀለሙ አመራረጥና ሌሎችም ሃይማኖታዊ የአሳሳል ደንባቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ትኩረትና ጥንቃቄ በማድረግ ይሳላል፡፡ ሥዕሉን ከመሳል ባሻገር ሃይማኖተዊ ተምሳሌቶች ለስዕሉ መሳያ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ወደ ሌላም እውቀት ሊሸጋገሩ የሚችሉ ናቸው። ስለዚህ የሥዕል መሳል ጥበቡ ሲጠፋ የተለያዩ እውቀቶች አብረው ይጠፋሉ።

ለውጥ ከሚታይባቸው ንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ሥዕል ነው። ለውጡም በውጭ ሀገራት በወረቀት እና በተለያዩ ቁሶች ላይ ተስለው የሚመጡ ስዕላት በሀገር በቀል እውቀት ይሳሉ የነበሩትን ስዕላት ቦታ እየያዙ ይገኛሉ። የወረቀት ሥዕሎቹ የአሳሳል ጥበብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን የሥዕል አሳሳል ደንብ ከመከተል ይልቅ ሥእሎቹን ስለው የሉኩትን ሀገራት ባህል ተከትለው የተሳሉ ናቸው፡፡ በወረቀት እና በሌሎች ቁሶች ላይ ከሚሳሉትው በተጨማሪ ሥዕለ ቅዱሳንን በድንጋይና መሰል ማእድናት ላይ ቅርጽ መቅረጽ የቀለም ሥዕልን ቦታ ከያዙት መካከል ተጠቃሽ ነው። ለምሳሌ በእንጦጦ ማርያም የተቀረጸ ሥዕል ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ከንዋያተ ቅድሳት መካከል ባህላዊ እውቀትን መሠረት አድርገው ሃይማኖታዊ ይዘታቸውን እንደጠበቁ የሚሳሉ ስዕሎች ሙሉ በሙሉ ባለመቅረታቸው ሥዕል በከፊል እየተለወጡ ከሚገኙት ንዋያታ ቅድሳት አንዱ ነው።

የመስቀል ስራ በአካባቢው ከሚገኙ ጥሬ እቃዎች ከሚሰሩ ንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ሲሆን የመስቀል ቅርጽ የሚሰራበት ጥሬ እቃ የተለያየ ነው። መስቀሎች በተለያየ ቅርጽ እና መጠን ትውፊታዊውንና ሃይማኖታዊ ምሳሌያቸውን ጠብቀው ይሰራሉ። ሀገረሰባዊውን እውቀት ተከትለው የሚሰሩት መስቀሎች አይነት እንደ ቀድሞው ብዛት ባይኖረውም ሙሉ በሙሉ አልጠፋም። ከውጭ ሀገራት ተሰርተው የሚመጡ መስቀሎች ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መጥተዋል[7]። በአንጻሩ በአካባቢው ባሉ ቁሶች ያለ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ የሚሰሩ ሲሆን ዛሬም ድረስ የሚሠሩ ለምሳሌ እንደከበሮ፣ ጸናጸል እና መቋሚያ ያሉ ንዋያተ ቅድሳት በቀደመው አሰራር መንገድ የቀጠሉ ናቸው።

[7]ምንጭ፣ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ (ቃለመጠይቅ)።

የንዋያተ ቅድሳቱ ለውጥ ምክንያት የሚሰሩበት ጥሬ እቃ፣ የሰሪዎቹ እውቀት ትውፊታዊ ከነበረው ወደ ዘመናዊው ኢንዱስትሪ መሸጋገሩ እንዲሁም በውጭ ሀገራት የተሰሩትን አምጥቶ መጠቀም ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በንዋያተ ቅድሳቱ ላይ የሚታዩ ለውጦችን በቀጣዩ ንኡስ ርእስ ስር እንመለከታለን።

## 2.3 የንዋያተ ቅድሳት የለውጥ አይነቶች

የንዋያተ ቅድሳቱ አሰራር ላይ በየጊዜው የሚታየው ለውጥ የተለያየ መልክ አለው። ለውጡ በዋነኝነት በሚሰጡት አገልግሎት ሳይሆን የአሰራር ቅርጽ መለያየት፣ የሚሰሩበት ጥሬ እቃ የነበረው ቀርቶ በሌላ መተካት፣ ሀገረ ሰባዊ የነበረው የአሰራር ዘዴ ወደ ዘመናዊ ማሽን መለወጥ ዋነኞቹ የለውጥ አይነቶች ናቸው። በተለይ ንዋያተ ቅድሳቱ ሀገር ውስጥ መሰራታቸው ሲቀር ጥሬ እቃውም የአሰራር ጥበቡም አብሮ መለወጥን ብሎም መቅረትን ያስከትላል።

በንዋያተ ቅድሳት ላይ የሚታየው ሌላው የለውጥ አይነት ቀደም ሲል አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ንዋያተ ቅድሳት በሌላ መተካት እንዲሁም አዳዲስ ንዋያተ ቅድሳት እየተለመዱ መምጣት ናቸው። ለረዥም ዘመን ሲያገለግሉ የነበሩ ንዋያተ ቅድሳት እየቀሩ ቀደም ሲል ያለውን ተግባር በሚፈጽሙ አዳዲስ ንዋያተ ቅድሳት እየተተኩ መምጣት የሚስተዋል ለውጥ ነው፡፡ እነዚህን ለውጦች በሁለቱም መልክ ስናየው፤ አንደኛው ሙሉ በሙሉ በሌላ የተተኩ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ የቀሩ አገልግሎታቸውም የቀረና ስማቸው ጭምር በመረሳት ላይ ከሚገኙት መካከል ለምሳሌ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ ርካም[8]፣ አያሚን (ያሚን) ወይም ኩከም[9]፣ እብሪቅ (ኩስኩስት)[10]፣ ቀንአት[11]፣ ሙዳየ እፍረት[12]፣ በትረሐዲን[13] እንዲሁም በትረወርቅ[14] ይገኙበታል። እነዚህ ንዋያተ ቅድሳት ዛሬ በቤተ-ክርስቲያን የማናገኛቸው ስማቸው ጭምር እየተረሳ የሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት ናቸው። አዳዲስ እየተለመዱ ከሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ለምሳሌ ታቦት ማንሻ፣ታቦት ማክበሪያ የሚባሉ ለክብረ በዓል ታቦት የሚሸከመው ካህን የሚገለገልበት ይገኙበታል፡፡ ጳጳሳት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለአገልግሎት ሲሄዱ የሚቀድሱት በልብሳቸው ነበር። ዛሬ ግን ጳጳሳት ወደ ተለያዩ ኣብያተ ክርስቲያናት ሲሄዱ የቅዳሴ አገልግሎት የሚሰጡባቸውን መቀደሻ ልብስ ለብቻ ተዘጋጅቶ ይዘው መሄድ የተለመደ ሆኗል። አዳዲሶቹ ንዋያተ ቅድሳት መለመዳቸው

---

[8]ከእብነ በረድ ወይም ነጭ ድንጋይ የሚዘጋጅ ገልባጣ ጻሕል ነው። አገልግሎቱም ቁርባነ ኅብስት የሚቀመጥበት ነው። ዛሬ በሌላ ንዋየ ቅድሳት ተተክቶ ስሙም እየተረሳ ነው (አብይ 1963፡ 11)።

[9]የፍም የእሳት መጫሪያ ዲያቆኑ የሚገለገልበት ዛሬ መጫሪያ በሚል ተተክቷል (አብይ 1963፡ 27)፡፡

[10]ጉጠት ያለው ለቅዳሴ ጠበል መያዣ ያገለግል ነበር። አሁን ማንቆርቆሪያ ተብሎ የቅርፅ ለውጥ ተደርጎበታል።

[11]ለቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ከዕጣን ዕንጨት የሚቀመም ሽቱ ነበር። እንዲሁም ተመሳሳይ አገልግሎት የነበረው ጠርቴንቶስ (ቴሬቤንቶስ) የሚባል ሽቱ ነበር ዛሬ ግን የለም (አብይ 1963፡ 49)።

[12]ሙዳየ እፍረት የሚባለው ለቤተክርስቲያን የሚያገለግል ሽቱ ማስቀመጫ ነበር። እንደ ሽቱ የሚያገለግለው በዕጣን መልክ መጥቶ ጨሶ እንፋሎቱ ነበር። (አብይ 1963፡ 52)፡፡ ዛሬ በቤተ-ክርስቲያንም ሆነ በሌላ ቦታ የለም። ምክንያቱም አሁን ሽቶ የሚዘጋጀውና የሚታወቀው በፈሳሽ መልክ እንጂ በዱቄት መልክ አለመሆኑ ነው።

[13]ከብር የተሠራ ዱላ ካህናት የሚይዙት (አብይ 1963፡ 59)። ዛሬ ከብር የተሠራ የለም፣ስሙም አይታወቅም።

[14]ከወርቅ የሚሠራ በትር ከፍ ያለ ሥልጣን ያላቸው የቤተክህነት ሰዎች የሚይዙት (አብይ 1963፡ 62)።

ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቢመጣም እነዚህ ሕግ ያልወጣላቸው ንዋያተ ቅድሳት ምናልባት እየተለመዱ ሲሄዱ ቀኖና ይወጣ ይሆናል፡፡

በንዋያተ ቅድሳት አሠራር ትርጉምና ምሳሌ ላይ የሚታዩት እና መስሪያ ቁስ ላይ የሚታዩ ለውጦች በየዘመኑ የሰው ልጅ የሚፈጥራቸው አዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች አስተዋፅዖ አላቸው፡፡ በተለይም ከለውጡ አይነት አንዱ የሆነው ሀገር ውስጥ በሀገረ ሰባዊው እውቀትና በአካባቢው ከሚገኙ ቁሶች ይሰሩ የነበሩ ንዋያተ ቅድሳት ከውጭ ሀገራት መምጣት የሚጠቀስ ነው። ንዋያተ ቅድሳቱ የሚሰሩበት ጥሬ እቃ ከውጭ ሀገራት ከሚመጡት መካከል በተለይ ልብሰ ተክህኖ፣ ከእንጨት እና ከብረት ነክ ማእድናት የሚሰሩ ንዋያተ ቅድሳት ይገኙበታል። ለዚህ ለውጥ እንደምክንያት የሚጠቀሰው ንዋያተ ቅድሳቱ የሚገዙት በአብያተ ክርስቲያናት የሃይማኖት መሪዎችና በአገልጋዮቹ ብቻ ሳይሆን በምእመናንም ጭምር መሆኑ ነው። ምእመናን ለውጭው ዓለም ቅርብ መሆንና ለሌላው ዓለም ያለው አዎንታዊ አመለካከት ለለውጡ በምክንያትነት ይጠቀሳል።

በተለይ ምእመናን በስጦታ መልክ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚሰጡት ንዋያተ ቅድሳት በአብዛኛው ለውጥ የሚታይባቸው ናቸው። የቁሶቹ ከውጭ ሀገራት መምጣት በአምጪዎቹ እና ገዝተው ለቤተ-ክርስቲያን በስጦታ በሚሰጡ ግለሰቦች አመለካከት "የተሻለ ንዋያተ ቅድሳት ከውጭ ሀገራት የሚመጣው ነው" ብሎ ማሰብ ነው[15]። ለዚህ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው እና በምልከታም ለማረጋገጥ የተቻለው በተለይ በትልልቅ በአላት ላይ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ደጃፍ በነጋዴዎች ለሽያጭ የሚቀርቡ ንዋያተ ቅድስትን የተሻሉ ናቸው ለማለት የሚጠቀሙባቸው የተለመደ ማስታወቂያ "ከኢየሩሳሌም የመጡ ንዋያተ ቅድሳት" የሚል ነው። እነዚህን ንዋያተ ቅድሳት ምእመኑ በብዛት በመግዛት ለየአብያተ ክርስቲያኑ ይሰጣሉ[16]።

በንዋያተ ቅድሳቱ አሰራር ላይ በየዘመኑ በተለያየ ምክንያት ለውጦች ታይተውባቸዋል።የይዘትና የቅርጽ ለውጥ ያመጡ ንዋያተ ቅድሳት ለውጥ በሚሰጡት አገልግሎት ሳይሆን የአሰራሩ መለያየት እና በተለይ ትውፊታዊ የነበረው የአሰራር ዘዴ መቅረት የለውጥ ምክንያት ነው። ከለውጡ መካከል ትውፊታዊ የሆነው የንዋያተ ቅድሳት ስራ ወደ በዘመናዊው የአሰራር ስልት መተካት ዋንኛው ነው። ሌላው የለውጥ ምክንያት በትውፊታዊው እውቅት የሚሰሩትን ንዋያተ ቅድሳት ሙሉ በሙሉ በመተው ከውጭ ሀገር ማምጣትና በቀጥታ አገልግሎት ላይ ማዋል በጥናቱ ከተገኙ የለውጥ ምክንያቶች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው።

በንዋያተ ቅድሳት ላይ የተከሰተው ለውጥ በቁሳዊ ባህሉ ላይ የሚታይ ለውጥ ነው። በባህል ላይ የሚታዩ ለውጦች ተፈጥሯዊ እና ሙሉ በሙሉ የባህሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ ሊከላከለው የሚችልም አይደለም። ሆኖም በለውጥ ውስጥ ሌሎች ባህላዊ እውቀቶች አብረው እንዳይጠፉ ብሎም እንዳይከስሙ መቆጣጠር ያስፈልጋል። የቁጥጥሩም ስልት ቀድሞ የነበረው የአሰራር ዘዴ እንዳለ ሆኖ እንደየዘመኑ የሚሻሻሉት ሲሻሻሉ የቀደሙት ተመዝግበው የሚቀመጡበት መንገድ ማመቻቸት ተገቢ ይሆናል። በንዋያተ ቅድሳት ላይ የሚታዩ ለውጦች ላይ ሊተኮርበት የሚገባው

[15]ምንጭ መምህር ፍስሐጽዮን ሀምሳሉ (ቃለ መጠይቅ)።

[16]ምንጭ መምህር ሊቀ ልሳናት ከፍያለው በላይ (ቃለ መጠይቅ)።

ለእውቀት መሰረቱ ባህል ወይም ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን አንዱ ከሌላው ይወስዳል በሂደት እየተደጋገፈ፣ እየተወራረሰ አንዱ ሌላውን ያበለጽጋል። በተለይም የኢ.ኦ.ተ.ቤ እንደማንኛውም የክርስትና ሃይማኖት መሠረቷ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሆኖም በርካታ ኢትዮጵያዊ መልኮች ይታዩበታል። የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳቱን ከሕንጻ ቤተ-ክርስቲያን ጀምራ ስትሰራ ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ሁሉ ንዋያተ ቅድሳቱን እንደተሰሩ ከሌላው ዓለም አልተቀበለችም። የተጻፈውን የሃይማኖት መሰረት ይዛ በአካባቢው ከሚገኙ ባለሙያዎች እና በቅርብ ከሚገኙ ጥሬ እቃዎች ሰርታለች። በተለይ የዜማ ንዋያተ ቅድሳት የሆኑት ከበሮ ጸናጽል እና መቋሚያ ሀገር በቀል የሆኑ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብቻ ናቸው። አብዛኞቹ ንዋያተ ቅድሳት አሁን ባሉበት ደረጃ የንዋያተ ቅድሳቱ የአሰራር ባህላዊ እውቀት እየከሰመ፤ ሃይማኖታዊ ቀኖናቸው በለውጥ ላይ ይገኛል።[17]

### 3. መደምደሚያ

በአጠቃላይ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ንዋያተ ቅድሳት የምንላቸው በጥቅሉ ከሕንጻ ቤተክርስቲያኑ ጀምሮ መገልገያ ቁሶቹን በሙሉ ነው። አሰራራቸውን ስንመለከት መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ይሁን እንጂ የአሰራሩን መመሪያ አንብበው በተግባር የሚሰሩት የሃይማኖቱ ተከታዮች ወይም ጥበቡ ያላቸው ግለሰቦች ናቸው። የንዋያተ ቅድሳቱን ትውፊታዊ መሆን በተለይ ከቁሳዊ ባህልነታቸው ጋር በማያያዝ ስንመለከት ቀደም ሲል ሙሉ በሙሉ በሀገር በቀሉ እውቀት የሚሰሩ ነበሩ። ሆኖም በሂደት በዘመናዊ መልኩ በሚሰሩት እንዲሁም በውጭ ሀገራት ተሰርተው በሚመጡ እየተለወጡ ይገኛሉ። የንዋያተ ቅድሳቱን ለውጥ  አንዳንዶቹ  ሙሉ በሙሉ ስማቸው ጭምር እየተረሱ የሚገኙ፤ ቀድሞ ያልነበሩና በስምም ሆነ በአገልግሎት የማይታወቁ አዳዲስ ንዋያተ ቅድሳትም የለውጡ አካል ሆነዋል። የንዋያተ ቅድሳቱ የለውጥ ምክንያት ከሆኑት መካከል ሀገር በቀሉ ጥሬ እቃና እውቀት በውጭ ሀገር ጥሬ እቃና የአሰራር እውቀት እየተተካ መምጣት ይገኝበታል። ከውጭ ሀገራት የሚመጡ ንዋያተ ቅድሳት ለውጡ የቅርጽና የሚሰሩበት ጥሬ እቃ ላይ ብቻ የሚታይ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ሀገረ ሰባዊውን እውቀት የሚያጠፋ ነው።

በትውፊታዊው እውቀት በሀገር በቀል ጥሬ እቃ ይሰሩ የነበሩትን ከውጭ ሀገራት በሚመጡት በመተካት ከተለወጡት ንዋያተ ቅድሳት መካከል ለምሳሌ ልብሰ ተክህኖ አንዱ ነው። ቀደም ሲል የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ትገለገልበት የነበረውን በሀገር በቀሉ እውቀት የተሰራውን ልብሰ ተክህኖ በየዘመኑ ምቹ እንዲሆኑ ባለሙያዎቹን እያበረታታች እና ስራዬ ብላ በመከታተል እውቀቱ ቢዳብር ኑሮ ዛሬ ሙሉ በሙሉ ከውጭ በሚመጡት ልብሶች ንዋያተ ቅድሳት አይለውጡም ነበር።

ለትውፊታዊው እውቀት መዳበር አስተዋጽዎ ማድረግ ይችሉ የነበሩ ሀገር ውስጥ የተሰሩትን ቁሳዊ ሀብቶች ወደ ውጭ ሀገራት መላክም ይቻል ነበር። ሆኖም በተቃራኒው በትውፊታዊው እውቀት ይሰሩ የነበሩትን ንዋያተ ቅድሳት በመተው ከውጭው ሀገር በሚመጡት መተካት እየተለመደ መጥቷል። እነዚህ ንዋያተ ቅድሳት በርካታ ባለሙያዎችን በስራው ላይ ማሳተፍ የሚችሉ የስራ

[17]ምንጭ መምህር ፍስሐ ጽዮን ሀምሳሉ (ቃለ መጠይቅ)።

መስክ መፍጠር ይችሉ ነበር። ንዋያተ ቅድሳቱ ለኢ.ኦ.ተ.ቤ ወሳኝ እና ቤተክርስቲያኗ እስካለች ሁሌ የሚያገለግሉ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኗ ንዋያተ ቅድሳቱን የምትፈልጋቸው ለአምልኮ ሥርዓት መፈጸሚያ እንጂ ትውፊታዊው እውቀቱን ማዳበር ዋና ጉዳዩዋ ስለሆነ አይደለም። ሆኖም ከውጭ ሀገራት የሚመጡ ንዋያተ ቅድሳት የሚያመጡት ለውጥና አሉታዊ ተጽእኖ በሀገር በቀሉ እውቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በኢ.ኦ.ተ.ቤ ቀኖና ላይ ጭምር ነው። ለምሳሌ ከሥዕላት ጋር ተያይዞ ሥላሴ በሀገራችን የሚሳሉበትና በአውሮፓውያን የሚሳሉበት ፈጽሞ የተለያየ ነው። አሁን የሥላሴ ሥዕል በሀገራችን ሳይሆን በአውሮፓውያኑ የአሳሳል ደንብ የተሳሉ ናቸው። የሀገራችን ትውፊታዊ እውቀት በሃይማኖት ሰበብም ሆነ በሌላ ምክንያት መዳበሩ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት። ስለዚህ እነዚህን ለውጦች በተለይም የሀገር በቀሉን እውቀት በውጭ የመተካት ሂደት ባለበት እንዳይቀጥል የኢ.ኦ.ተ.ቤ እንዲሁም የባህል ተቋማት ስለ መፍትሄው ማሰብ ይገባቸዋል።

በተለይ የኢ.ኦ.ተ.ቤ በቀኖናው መሠረት የራሷ ንዋያተ ቅድሳት ማምረቻ እና ማከፋፈያ ሊኖራት ሲገባ አለመኖሩ ለለውጡ ምክንያት ሆኗል። በዚህ ምክንያት አሁን ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ንዋያተ ቅድሳት ለማዘጋጀት ከብረት ነክ መአድናት የሚሰሩትን ከብረት ባለሙያ ዘንድ፣ ከእንጨት የሚሰሩትን ከእንጨት ባለሙያ፣ ከስንደዶና መሰል ጥሬ እቃ የሚሰሩትን እንዲሁ ከሌሎች ባለሙያዎች ዘንድ የሚሰባሰቡ ሆነዋል። የኢ.ኦ.ተ.ቤ ይህንን የተበታተነ ቦታ ያሉ ባለሙያዎችን በአንድ በማደራጀት ቀኖናውን ተከትለው እንዲሰሩ ተቋማትን በብዛት ብታቋቁም ከሃይማኖታዊ ጠቀሜታው ባሻገር የተለያዩ ሀገራዊ ጠቀሜታዎች ማበርከት ትችላለች። አልያም የተለያዩ የመንግስት ተቋማት እንደ አንድ ተቋም ባለሙያዎቹን ቢያደራጅ ቤተክርስቲያኗ ለሃይማኖቱ የሚሆናትን ጥሬ እቃ ታገኛለች። ባለሙያዎቹ ደግሞ ስራቸውን በመስራት የገቢ ምንጭ፣ እውቀት ማዳበሪያ የተሻለም ፈጠራ የሚያመጡበትን አጋጣሚ ይፈጥራል። በዚህም የቁሳዊ ባህል ዘርፍ የመስራት እውቀት በማህበረሰብ ውስጥ እያደገ ይሄዳል።

## ዋቢ ጽሁፎች


ሀብተማርያም ወርቅነህ። 1963። *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ሉሌ መልአኩ። 1986። *የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ*። አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት።

ነጋሽ በቀለ። 1988። *"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ትምህርት አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ።"* ያልታተመ።

አስኳል አማረ። 1994። *ንዋያተ ቅድሳት ለአገልግሎት ሊያውሏቸው ይገባልን*። ሐመር መጽሄት። አዲስ አበባ ብራና ማተሚያ ቤት።

ዐብይ ፍትህ አወቀ። 1963። *"የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳትና የአልባሳት ስሞች"*። ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ።

ከንፈ ገብርኤል አልታዬ። 1992። *ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን*። አዲስአበባ። ትንሣኤማተሚያድርጅት።

ከንፈገብርኤልና ጌታቸው። 1998። *ሥርዓተቤተ ክርስቲያን*። አዲስአበባ ትንሣኤማተሚያቤት።

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። 1980። *መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻህፍት)*። አዲስአበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዴሚ። 2006። *የአማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ማተሚያቤት።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን። 1994። *የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ትላንትና ዛሬና ነገ።* አዲስ አበባ ሜጋ ማተሚያ ኢንተር ፕራይዝ።

ያሬድገ/መድህን። 1996። *ኖኅተ ሰማይ*። አዲስአበባ። ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

ፍሬሕይወት ባዩ። 2000። *"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ"*። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ በኢትዮጵያ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

*ፍትሐ ነገሥት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ*። 1956። *አሥመራ*። ኮከበ ጽባህ ማተሚያ ቤት።

Dorson, Richard. 1972. *Folklore and Folk Life: An Introduction*. London. University Press of Kentucky.

Glassie, Henry. 1999. *Material Culture*. Blomington and Indianapolis: Indiana University press.